# <u>የዮሐንስ መልዕክት (26)</u>

## <u>ጥናት አንድ (1ኛ ዮሐ 1፡1-10)</u>

የጥናት ዓላማ፡ የደህንነትን ወንጌል አማኝ ለሌሎች በማብሰር በክርስቶስ በማመን ያገኘውን ደስታ የተሟላና የተትረፈረፈ ማድረግ እንደሚችል ለማየት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እናንተም ከእኛ ጋር ህብረት እንዲኖራችሁ…ደስታችንም ፍጹም ይሆን ዘንድ ይህን እንጽፍላችኋለን፡፡›› 1ኛ ዮሐ 1፡3-4

1. 1ኛ ዮሐ 1፡1-10 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ውስጥ ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የተጠቀሰ አንድ ቃል ምንድነው? የዮሐንስ ወንጌልና 1ኛ ዮሐ አጀማመር በምን መንገድ ይመሳሰላል?
2. በቁ1 ላይ እናውቛለን ብለው የሚናገሩት ምንን ነው? ይህ የታየው፣ የተሰማውና የተዳሰሰው ምንድነው ይላሉ? ይህ የዮሐንስ አነጋገር ስለ ነገሩ እውነትነት ምን ይነግረናል?
3. ዮሐንስ ይህንን የህይወት ቃል ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን የተለያዩ አገላለጾች ዘርዝር፡፡
4. ሐዋርያው ዮሐንስ እነርሱ ያዩትን፣ የሰሙትንና የዳሰሱትን ለአንባቢዎቹ ስለሚጽፍባቸው ምክንያቶች ምን ይናገራል?
5. በቁ5-10 መሰረት ፀሐፊው በመልዕክቱ ማስተላለፍ የፈለገውን እውነት በአንድ ዓረፍተ ነገር ተናገር ብትባል መልስህ ምን ይሆናል?
6. በቁ5-10 ውስጥ ‹‹ብንል›› የሚለው ቃል ስንት ጊዜ ሰፍሮ ይገናል? እያንዳንዱን በምን ዓይነት መንገድ እንደተጠቀመባቸው ተናገር፡፡
7. በቁ5 ላይ ዮሐንስ ስለሚጽፈው መልዕክት የሚናገራቸውን ሃሳቦች ሁሉ ዘርዝር፡፡
8. በቁ5 ላይ የወንጌሉን እውነት የምናውጅበት ምክንያት ብለው ‹‹ደስታችን ፍጹም ይሆን ዘንድ›› ሲሉ ምን ማለት ይመስልሃል? የወንጌልን እውነት በማወጅ ደስታህ ፍጹም ሊሆን እንደሚችል አስበህ ታውቃለህ ወይ? ወንጌልን ለሌሎች ማካፈል ለሰሚው ብቻ ሳይሆን ለተናጋሪውም የደስታ ምንጭ ስለሆነ ከመናገር ዝም አትበል፡፡

# ጥናት ሁለት (1ኛ ዮሐ 2፡1-6)

የጥናት ዓላማ፡ የእግዚአብሄር ፍቅር በአማኝ ህይወት ውስጥ ፍጹም የሚሆነው ቃሉን ከማወቅ አልፎ በህይወቱ ሲታዘዘው መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሄር ፍቅር በእርሱ ፍጹም ሆኖአል፡፡›› 1ኛ ዮሐ 2፡5

1. 1ኛ ዮሐ 2፡1-6 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዮሐንስ መልዕክቱን የጻፈው ለማን ነው? መልዕክቱን ስለጻፈበት ምክንያትስ ምን ይላል?
2. በቁ1-2 ባለው ውስጥ ሃጥያትን በተመለከተ ልንረዳ የሚያስፈልጉን ሁለት ዋና ዋና እውነቶች ምንና ምንድናቸው?
3. በቁ1-2 ውስጥ ስለ ኢየሱስ የምትገነዘባቸውን ሃሳቦች በሙሉ ዘርዝር፡፡
4. በቁ3 ላይ ‹‹እኛ›› እያለ የሚናገረው ስለነማን ነው? ‹‹እርሱ›› የሚለውስ ማንን ነው? በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስን አውቄዋለሁ የማለት ማረጋገጫ አድርጎ የተጠቀመው ምንን ነው?
5. ቁ3-6 ውሸተኛ በመባል የተነገረለት ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው? ከውሸታምነት ሌላ ስለዚህ ሰው ክፍሉ ምን ይናገራል?
6. በ1፡4 ላይ የአማኝን ደስታ ፍጹም የሚያደርገው ወንጌልም ማወጅ ሲሆን በ2፡5 ደግሞ የእግዚአብሄርን ፍቅር በአማኝ ህይወት ሙሉ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
7. በቁ3-6 ውስጥ በጌታ በየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ለመሆናችን በማረጋገጫነት የተነገረው ነገር ምንድነው? የኢየሱስ አረማመድ ምን እንደሚመስል ተወያዩበት፡፡
8. በቁ5 ላይ የእግዚአብሄር ፍቅር በህይወቱ ፍጹም ይሆናል ሲል ምን ማለቱ ነው? ቃሉን በመታዘዝ ምንያህል ለእግዚአብሄር ያለህን ፍቅር ታረጋግጣለህ/ፍጹም ታደርጋለህ? ለቃሉ መታዘዝ የፍቅርህን መጠን ስለሚለካ መታዘዝን የህይወትህ ልምምድ አድርገው፡፡

# ጥናት ሶስት (1ኛ ዮሐ 2፡7-17)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄርን ማወቃችን ትዕዛዙን በመጠበቃችን ሲታወቅ (1ኛ ዮሐ 2፡3)፣ ትዕዛዙን መጠበቅ አለመጠበቃችንን የምንመዝንበት ዋነኛው መንገድ ደግሞ ወንድማችንን ወይም እህታችንን የምንወድ አለመውደዳችን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙን ግን የሚጠላ አሁንም በጨለማ ውስጥ አለ፡፡ ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል…የማሰናከያ ምክንያት የለውም፡፡›› 1ኛ ዮሐ 2፡9-10

1. 1ኘ ዮሐ 2፡7-17 በአንድነት አንብቡት፡፡ ቁ7ትን በማንበብ ይህ ክፍል ስለተጻፈላቸው ሰዎች ምን ማወቅ እንችላለን? በዚሁ ቁጥር ስለመልዕክቱስ ምን መረዳት እንችላለን?
2. ቁ7 እና ቁ8 የሚቃረኑ የሚያስመስላቸውን ሃሳብ ተናገር፡፡ ትዕዛዙን አዲስ የሚያደርገው ነገር ምን ሊሆን ይችላል ትላለህ?
3. በቁ9-11 ውስጥ ጸሐፊው በማነጻጸር የሚያስተምረን ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው?
4. ከላይ ያየነው ክፍል ወንድሙን ስለሚጠላ ሰው የሚናገራቸውን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡ ወንድሙን ስለሚወድ ሰውስ ምን ይናገራል?
5. ቁ12-14 ለልጆች፣ ለአባቶች፣ እንዲሁም ለጎበዛዝት ለምን እንደሚጽፍ ተናገር፡፡ በተለይም በቁ14 ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ የጎበዛዝቱን ክፉውን ማሸነፍ ከምን ጋራ ነው ያያያዘው?
6. በቁ15-17 ባለው ክፍል ውስጥ በብዛት በተደጋጋሚነት የሰፈረው አንድ ቃል ምንድነው? ሐዋርያው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሊናገር የፈለገውን ሃሳብ በአንድ አጠር ያለ አረፍተ ነገር በመጠቀም ሃሳቡን ተናገር፡፡
7. በቁ15-17 መሰረት በአለም ያሉትን ነገሮች የጠቀለለባቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? በዚህ ክፍል ‹‹ዓለም›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው?
8. ዛሬ ባነበብነው ክፍል ስታይ፣ አማኝ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ መፈጸሙን ለማወቅ ራሱን መጠየቅ የሚችለው አንዱና ዋነኛ ነው የምትለው ጥያቄ ምንድነው? ዘሬ አንተ ራስህን ይህንን ጥያቄ ስጥጠይቅ ልብህን የሚከስህ ነገር አለ ወይ? ካለ ጊዜ ሳትሰጥ ዛሬውኑ ነገርህን አስተካክል፡፡

# ጥናት አራት (1ኛ ዮሐ 2፡18-29)

የጥናት ዓላማ፡ እኛ በክርስቶስ ያመንን ቅዱሱን ቅባት በውስጣችን ስላለ ሌላ ሃይል ለመቀበልም ሆነ ለአገልግሎታችን ስኬታማነት የሚንቀባው ተጨማሪ ቅባት ልንጠብቅ እንደማይገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ ቅባት አላችሁና ሁላችሁም እውነትን ታውቃላችሁ፡፡ …እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና›› 1ኛ ዮሐ 2፡20፣ 27

1. 1ኛ ዮሐ 2፡18-29 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ18 ላይ ‹‹የክርስቶስ ተቃዋሚ›› እና ‹‹የክርስቶስ ተቃዋሚዎች›› በሚሉት መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ ግለጽ፡፡
2. በቁ19 ውስጥ ብቻ አራት ጊዜ ‹‹እኛ›› የሚለውን ቃል እናያለን፡፡ ይህ እኛ የሚጠቁመው ማንን ነው? ‹‹ወጡ››፣ ‹‹አልነበሩም››፣ ‹‹ተለዩ›› እና የመሳሰሉትስ ቃላት ስለማን ነው የሚናገሩት?ማለት ሰው ከአንድ አጥቢያ ቤ/ክ ለቆ ወጣ ማለት ቀድሞውንም አላመነም ማለት ነው ወይ?
3. በቁ20-23 ላይ እናንተ ግን በማለት የሚያወዳድረው ማንንና ማንን ነው? በዚህ ቁ20-23 ላይ የተጻፈላቸውን  ሰዎች ከሌሎቹ የሚለዩአቸውን ሁለት ነገሮች ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ
4. በቁ21 ላይ ያለው ሲናገር፤ ለምንድነው እውነትን ለሚያውቁ እንጂ ለማያውቁ አልጽፍም የሚለው?
5. ከላይ በተመለከትናቸው አራት ቁጥሮች ውስጥ አንድን ሰው በሙሉ እርግጠኛነት ሐሰተኛ ነህ ብለን ለመናገር የሚያስደፍረን ምን ሲሆን ነው? ከዚህ ክፍል በወልድና በአብ መሃል ስላለው ሁኔታ ምን ያረጋግጥልናል?
6. በቁ26-27 ስለ ቅባቱ የሚናገራቸውን እውነቶች ዘርዝር፡፡ ይህ ከጌታ የተቀበልነው ቅባት በውስጣችን የሚሰራውና በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው አንድ ሥራው ምንድነው? ‹‹ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም›› የሚለውን ሃሳብ፤ አንዳንዶችን አስተማሪዎች አድርጎ ለቤተ ክርስትያን ሰጠ ከሚለው እውነት ጋራ አብሮ ማስኬድ የሚቻለው እንዴት ነው?
7. በተለይም በቁ27 ላይ እንዳስተማረን በእርሱ እንድንኖር ሲያደፋፍረን ምንን ተመርኩዞ ነው? ቁ28 ላይስ በእርሱ ለመኖር ተጨማሪ ማበረታቻ የሚሆኑ የምናነባቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. በቁ27 ‹‹እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራል›› በዚህ ጥቅስ ስትመረምረው አንድ ወንድም/እህት፡ ቅባት እንድትቀበል ልጸልይልህ  ቢልህ መልስህ ምን ይሆናል? ለምን? የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ስለሰጠን ሌላ የምንጠብቀው ቅባት አይኖርም፡፡ 2ኛ ቆሮ1፡21 ተመልከት፡፡

# ጥናት አምስት (1ኛ ዮሐ 3፡1-10)

የጥናት ዓላማ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ሰዓት ለማየትና የልጁን መልክ ለመምሰል ተስፋ የሚያደርግ ሰው ሁሉ ኢየሱስ ንጹህ እንደሆነ በንጽህና ሊኖር እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በእርሱ ይህንን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹህ እንደሆነ ራሱን ያነጻል፡፡›› 1ኛ ዮሐ 3፡3

1. 1ኛ ዮሐ 3፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ለእግዚአብሔር ፍቅር ትልቅነት ማረጋገጫ ሆኖ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሃሳብ ምንድነው? በዚሁ ቁጥር ላይ ዓለም እኛን አያውቀንም ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ቁ2 ‹‹አሁን የእግዚአብሄር ልጆች ነን›› ይላል፡፡ ክፍሉ ወደ ፊት ስለምንሆነው ሁኔታስ የሚናገረው ነገር ምንድነው? የወደፊቱን በተመለከተ ዛሬ በእርግጠኛነት የምናውቃቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
3. ቁ3 ላይ ‹‹ይህን ተስፋ የሚያደርግ›› የሚለው ስለየትኛው ተስፋ ነው የሚናገረው? ከላይ የተመለከትነው ተስፋ በምን ዓይነት ህይወት እንድንመላለስ ነው የሚያደፋፍረን?
4. በቁ5 ላይ ‹‹እርሱ›› የሚለው ማንን ነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ እርሱ ስለሚለው ሰው የተናገሩትን ሁለት እውነቶች ዘርዝር፡፡
5. በክርስቶስ ውስጥ ስለሚኖር ሰው ቁ6 የሚናገረው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ ‹‹ሃጥያት አያደርግም›› የሚለው ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡
6. ቁ9-10 ሲነበብ ለምንድነው ይላል ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው ሃጥያት ሊያደርግ (በሃጥያት ሊኖር) የማይችለው?
7. በቁ10 መሰረት የዲያቢሎስንና የእግዚአብሔርን ልጆች የሚለዩአቸው ሁለቱ ዋና ዋና ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
8. የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ስትጠባበቅ ሊኖርህ ስለሚገባው ህይወት ከዛሬው ትምህርት ምን ትማራለህ? ምጽአቱን መጠበቅ አንዱ ነገር ሲሆን ህይወትን ደግሞ በንጽህና መጠበቅ አብረን ልናስኬዳቸው የሚገቡ እውነቶች ናቸው፡፡

# ጥናት ስድስት (1ኛ ዮሐ 3፡11-24)

የጥናት ዓላማ፡ ተግባርና እውነት ያልተጨመረበት እወድሃለሁና እወድሻለሁ ብቻውን ፍሬቢስ ነገር መሆኑን በመረዳት ወደ እውነተኛና መስዋዕትነትን ወደ ሚጠይቀው ወደ ክርስቶስ ፍቅር ማደግ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ልጆች ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ››    1ኛ ዮሐ 3፡18

1. 1ኛ ዮሐ 3፡11-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11-15 እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያው ሰምታችሁታል የሚላቸው ትዕዛዝ ምንድነው? ይህንን ትዕዛዝ በመተላለፍ የመጀመሪያ የሆነው ሰው ማነው? ይህ ሰው አለመውደዱን ያረጋገጠበት ድርጊት ምን ነበረ?
2. ቁ13 ‹‹ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ›› ሲለን ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? ከሞት ወደ ህይወት የመሸጋገር አንዱ መለኪያ ምንድነው?
3. በቁ16 መሰረት የፍቅርን ምንነት በምን እናውቃለን ነው የሚለው? በዚህ ቁጥር አነጋገር እኛስ ህይወታችንን ለምንድነው ለወንድሞቻችን መስጠት የሚኖርብን?
4. ቁ17-18 ላይ በተጨባጭ መንገድ ለወንድሞቻችን ራሳችንን መሰጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የምናየው እንዴት ነው? ‹‹ሃብት እያለው›› ሲል ምን ያህል ገንዘብ ያለውን ሰው ነው ሃብት ያለው የሚለው?
5. ‹‹በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ፡፡›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሰፋ አድርጋችሁ ምሳሌዎች በመስጠት ተነጋገሩባቸው፡፡ እዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹ብቻ›› የሚለው ቃል ምን ይጠቁመናል?
6. በተግባር ለሚያስፈልጋቸው ወንድሞቻችን መድረሳችን በህይወታችን ውስጥ ስለሚያስከትላቸው ነገሮች ይህ ክፍል ምን ይናገራል?
7. በቁ21-24 መሰረት ከእግዚአብሄር የምንለምነውን ለመቀበል ቅድመ ሁኔታ ሆነው የቀረቡት ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ትዕዛዞቹን መጠበቅ አንዱ ቅድመ ሁኔታ ከሆነ እነዚህ ትዝዛዝ የተባሉት ነገሮችስ የትኞቹ ናቸው?
8. ኢየሱስ ክርስቶስ በምን መንገድ ነው በተግባርና በእውነት የመዋደድ ምሳሌ ሆኖ ሊቀርብ የምችለው? አንተስ ለወገኖችህ የምታሳየው የቃልና የአንደበት ወይስ የተግባርና የእውነት ፍቅር ይሆን? የኢየሱስን ምሳሌ ተከተል፡፡

# ጥናት ሰባት (1ኛ ዮሐ 4፡1-6)

የጥናት ዓላማ፡ እኛን ካላመኑት ሰዎች የሚለየን ነገር ስለክርስቶስ የምናምነው ትምህርት እንደሆነ ቢታወቅም አኗኗራችንና አነጋገራችንም ከእውነት መሆናችንን የሚናገሩ ሊሆኑ እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ዓለምም ይሰማቸዋል፡፡ እኛ ከእግዚአብሄር ነን፤ እግዚአብሄርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሄር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ በዚህም የእውነትን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ እናውቃለን፡፡›› 1ኛ ዮሐ 4፡6

1. 1ኛ ዮሐ 4፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ እንዳያደርጉ የሚያዛቸውና አንድ ደግሞ እንዲያደርጉ የሚያዛቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ ላዘዛቸው ትዕዛዛትስ በዚያው ክፍል ውስይ የሰጣቸው ምክንያት ምንድነው?
2. በቁ1-3 ውስጥ እነዚህ አማኞች እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ለመፈተን መጠቀም የሚችሉበት አንድ የሰጣቸው መለያ ምን ታያለህ? መመዘኛውን ያላሟላውን ሰው ከየትኛው ካምፕ ነው ጸሐፊው የሚመድበው?
3. ሐዋርያው በቁ3 ‹‹አሁንም እንኳን በዓለም አለ›› የሚለውስ ማንን ነው? በ2ኛ ተሰ 2፡1-12 የክርስቶስ ተቃዋሚን ወይም ሐሰተኛውን ክርስቶስ በመጨረሻው ዘመን እንደሚገለጥ ከነገረን ይህ አሁንም በአለም አለ የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ?
4. ቁ4-6 ላይ ‹‹እናንተ›› የሚለው እነማንን እንደሆነና ‹‹እነርሱ›› የሚለው ደግሞ እነማንን እንደሆነ ተናገር፡፡ በቅድሚያ እናንተ ስለሚላቸውና ቀጥሎ ደግሞ እነርሱ ስለሚላቸው ሰዎች የተናገራቸውን የተለያዩ ሃሳቦች አንድ በአንድ በመዘርዘር ተነጋገሩባቸው፡፡
5. በቁ4 ላይ እናንተ የተባሉት ሰዎች እነርሱ የተባሉት ሰዎችን ስላሸነፉበት ምክንያት የሚናገረው ነገር ምንድነው? በእነርሱ ያለው ማነው? በዓለም ያለውስ?
6. በቁ 6 ‹‹በዚህ የእውነትን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ እናውቃለን፡፡›› በዚህ የሚለው ቃል የሚጠቁመን የትኛውን ሃሳብ ነው?
7. ቁ1-6 ባለው ክፍል የእግዚአብሄርንና የሐሰተኛውን መንፈስ የምንለይባቸው ሁለት መንገዶች ይጠቁሙና፡፡ ቁ1-3 መመዘኛው በምን ላይ ያተኮረ ነው? ቁ4-6ስ ምን ላይ ያተኩራል?
8. ከእውነት ለመሆንህ የምታምነው ትምህርት ይመሰክርልሃ ወይ? ኑሮህና አነጋገርህስ ምን ያህል ምስክር ይሆኑሃል? በአብዛኛው ሰዎችን ለማመንህና ላለማመንህ ግራ የሚያጋባቸው ትምህርት ሳይሆን ኑሮህ ስለሆነ ኑሮህና ትምህርትህን በማዛመድ ለመመላለስ ትጋ፡፡

# ጥናት ስምንት (1ኛ ዮሐ 4፡7-21)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሔርን እመስላለሁ ወይም እወዳለሁ ለሚል አማኝ የቃሉን እውነተኛነት ለማረጋገጥ የሚችልበት አንዱና ብቸኛው መንገድ በፍቅር መመላለስ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እግዚአብሄር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሄር ይኖራል፡፡ በዚህ ዓለም እርሱን እንመስላለንና›› 1ኛ ዮሐ 4፡16-17

1. 1ኛ ዮሐ 4፡7፡21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ 7 ላይ ፍቅርን በተመለከተ የሚናገራቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው?
2. ዮሐንስ ለምንድነው የማይወድ ሰው እግዚአብሄርን አያውቀውም በማለት ደፍሮ የሚናገረው?
3. ቁ7-10 የኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት ከምን ጋራ ነው የሚያያይዘው? መምጣቱ ለእኛ የሚያስገኝልን ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
4. ቁ11 ስታነብ ከላይ የሰፈሩት ቁ7-10 ያሉትን ጸሃፊው ስለተናገረበት ምክንያት ምን ትረዳለህ?
5. ለእኛ አማኞች ቁ13-14 ሊያረጋግጥልን የሚችላቸውን ቢያንስ ሶስት ሃሳቦች ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል በህይወታችን የሥላሴዎችን ሥራ የተገለጠበትን መንገድ አንድ በአንድ አስረዳ፡፡
6. ሐዋርያው ዮሐንስ በቁ14 ላይ ሐዋርያቱንና አማኞችን በመወከል አስረግጦ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? እርሱ ያየውን አንተስ አይተሃል ወይ? ያየኸውንስ አውነት ትመሰክራለህ ወይ?
7. በፍርድ ቀን በሙሉ ድፍረት ልንቆም ስለሚያስችለን አንድ ነገር ቁ16-17 ይነግረናል፡፡ ይህ አንድ ነገር ምንድነው? ይህንን ለፍርድ ቀን ድፍረት ሊሆንል የሚችለውን ነገር ምን ያህል በህይወትህ ትለማመደዋለህ?
8. በቁ19-21 ስለ ፍቅር የሚናገራቸውን እውነቶች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
9. ቁ17‹‹በዚህ ዓለም እርሱን እንመስላለንና፤፤›› የሚለው አነጋገር በምን መንገድ ነው ‹‹እግዚአብሄርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል›› ከሙለው ሃሰብ ጋራ ሊያያዝ የሚችለው? በዚህ ዓለም እርሱን መምሰልህን ልታሳይ የምትሞክርበት ሌላ መንገድ ካለህ የተሻለው መንገድ የፍቅር መንገድ ነውና በዚያ መንገድ ግለጸው፡፡

# ጥናት ዘጠኝ (1ኛ ዮሐ 5፡1-21)

የጥናት ዓላማ፡ መሸሽ ሲገባን በመጋፈጥ ወይም ደግሞ ደግሞ መጋፈጥ ሲገባን በመሸሽ የማያስፈልግ ሽንፈት ውስጥ እንዳንገባ ውጊያችን ከማን ጋራ መሆኑን መረዳት እንደሚጠቅም ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በስተቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?›› 1ኛ ዮሐ 5፡4-5

1. 1ኛ ዮሐ 5፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1 ከእግዚአብሄር ለመወለድ ምልክት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው? በቁ1 ‹‹ልጁንም›› በቁ2 ደግሞ ‹‹ልጆች›› የሚሉት የሚናገሩት ስለ አንድ ሰው ነው ወይስ ይለያያሉ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
2. በቁ2 አባባል መሰረት ክርስትያኖችን ወይም የጌታን ልጆች ለመውደዳችን ማረጋገጫው ምንድነው ይላል? ላንተስ አማኞችን መውደድህን ልታረጋግጥ የምትሞክርበት መንገድ ምንድነው?
3. በቁ3-5 መሰረት ትዕዛዙን መፈጸም ከባድ ያልሆነበት ምክንያት ለምንድነው ይላል? ዓለም ሊሸነፍ የሚችለው በምንድነው? በዚህ ክፍል አጠቃቀም እምነት ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. በቁ6-12 ውስጥ ምስክርነት የሚለው ሃሳብ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል? ይህንን ክፍል ስታነብ በምስክርነቶች መሃል መበላለጥን ታያለህ ወይ? አስረዳ፡፡ እግዚአብሄር ስለ ልጁ የመሰከረበትን አንድ የምታስታውሰውን ክፍል ተናገር፡፡
5. ቁ13-15 በማንበብ መልዕክቱ ስለተጻፈላቸው ሰዎች ማንነት ምን እንረዳለን? ጸሐፊው ስለጻፈበትስ ምክንያት ምን ታያለህ?
6. በቁ18 ላይ ‹‹እናውቃለን›› የሚለው አነጋገር ያጠቃለላቸው ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? ከእግዚአብሄር የተወለደ ሁሉ ሃጥያት አያደርግም ሲል ፍጹማን ሆነናል ማለቱ ነው ወይስ ምን ማለቱ ነው?
7. ቁ19-20 ላይስ ‹‹እናውቃለን›› የሚላቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. በተራ ቁ 3 ላይ በእምነት ዓለምን ስለማሸነፍ የተነገረውን ሃሳብ በ2ኛ ጢሞ 2፡22 እና ያዕ 4፡7 ካሉት ሃሳቦች ጋራ በአንድነት በማየት አማኝ ሶስቱን ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ መንፈስ ቅዱስ ስላዘጋጃቸው  መንገዶች ምን ታያለህ? ውጊያህ ከማን ጋራ መሆኑን ማወቅህ ለምን ይጠቅማል ትላለህ? መሸሽ ሲገባህ ለመጋፈጥ እንዳትሞክር፣ መጋፈጥ ሲኖርብህ ደግሞ እንዳትሸሽ ጠላትህን እወቅ፡፡